የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0812/14
ቀን/Date መስከረም 2 5 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- **በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር ማስፈጸሚያ የአሠራር ስርዓት ስለመላክ፤**

ዕቃ በመያዝ ወደ ሀገር ውስጥ በጊዜያዊነት ገብቶ ተመልሶ ለሚወጣ ኮንቴነር በ2009 ዓ.ም በተላለፈ የአሰራር ስርዓት መሠረት ሲፈጸም የቆየ ሲሆን በአሰራር ስርዓቱ ላይ በሚመለከታቸው አካላት አስተያየት እና ግብዓት ተሰጥቶበት ለአፈጻም ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር በተዘጋጀው የአሠራር ስርዓት መሠረት በጥብቅ ዲሲፕሊን ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የፀደቀውን "በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር የማስፈፀሚያ የአሠራር ስርዓት" ሰነድ በኮሚሽኑ ዌብሳይት እና ኮሚሽኑ በሚጠቀምባቸው ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲያደርግ እየገለጽኩ፤ የሰነዱን ቅጅ 14 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No. 1

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋም አቀፍ ሥጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍና ሥሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ተገዥነትና ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>፣

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>**በያሉበት**</u>፣

ገ/ጽ/ሬት/659
ጋ/ፀ/A

ጉፅ 1179
07/13/13

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጉምሩክ ኮሚሽን
F.D.R.E. CUSTOMS COMMISSION
የውስጥ መገናኛ
INTERNAL OFFICE MEMORANDUM

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር፡ ጉኦዘ/6/475/13

→ ለ፡ ክቡር የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ከ፡ ጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ

አንዷለም ሜኔ አበበ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን
ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

ቀን፡ 29/12/2013 ዓ.ም.

ጉዳዩ፡- በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር ማስፈፀሚያ የአሠራር ስርዓትን ይመለከታል፤

ዕቃ በመያዝ ወደ ሀገር ውስጥ በጊዜያዊነት ገብቶ ተመልሶ ለሚወጣ ኮንቴነር በ2009 ዓ.ም. በተላለፈ የአሰራር ስርዓት መሠረት ሲፈፀም ሙቆየቱንና ተጨማሪ ማሻሻያ በማስፈለጉ ከኮሚሽኑ ውስጥና ከውጪ የሚመለከታቸው የንግድ ማህበረሰብ አስተያየት በማካተትና የነበረው የአሰራር ስርዓት በማሻሻል የተዘጋጀ በመሆኑ ማንዋሉ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ውሳኔ እንዲሰጥበት በውስጥ ማስታወሻ የቀረበ ቢሆንም በአሠራር ማንዋሉ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግበት ግብዓት የተሰጠ መሆኑ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት የተሰጡ አስተያየቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ተካተው የተዘጋጀ የአሰራር ማንዋል ስለሆነ ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል ውሳኔ እንዲሰጥበት 13 ገጽ አባሪ አያይዘን ለውሳኔ አቅርበናል፡፡

ግልባጭ/

- ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት /ያለአባሪ/
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት /ያለአባሪ/

ጉምሩክ ኮሚሽን

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission

ለም/ቦርድ ጉዳዩ

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs

**የውስጥ ማስታወሻ**

**INTERNAL MEMORANDUM**

ቁጥር:ዕቃ/69/2013
ቀን 28/12/2013

ገቢ 1593 28-12-13

**ለ: ኦፐሬሽን ዘርፍ**

**ከ፡ ንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት**

እንዳሻው ተመስገን በየነ
የንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና
ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

**ጉዳዩ፡-** **<u>በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር አሰራርን ይመለከታል፤</u>**

ዕቃ በመያዝ ወደ አገር ውስጥ በጊዜያዊነት ገብቶ ተመልሶ ለሚወጣ ኮንቴነር በ2009 ዓ.ም በተላለፈ የአሰራር ስርዓት መሠረት ሲፈፀም የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና

- በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ኮንቴነር በአገር ውስጥ የመቆያ የጊዜ ገደብ የሚራዘምበት ሁኔታ በግልፅ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤
- የዋስትና አያያዝ ስርአቱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ በተለያየ ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ ባላቸው እንደ ኤክስፖርት ባሉ  የስራ ዘርፎች ለተሰማሩ ድርጅቶች ያበለጠ ምቹ ለማድረግ፤
- ኤክስፖርት ላይ የተሰማሩ ላኪ ድርጅቶች የኮንቴነር ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ባዶ ወይም ዕቃ ሳይዝ ኮንቴነር በጊዜያዊነት ወደ አገር ማስገባት የሚቻልበት ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፤
- ኮንቴነር ተመልሶ ሲወጣ በሲስተም በማረጋገጥ ብቻ ዋስትና ተመላሽ የሚደረግበት ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤
- በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብተው ጉዳት የደረሰባቸው ኮንቴነሮች የሚያስተናግዱበት አግባብ በግልፅ ማመላከት በማስፈለጉ፤
- ዕቃ ይዞ ወደ አገር የገባ ኮንቴነር በአገር ውስጥ ለዕቃ ላኪ ወይም ለመርከብ ወኪል በማስረከብ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ የሚቻልበት ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከኮሚሽኑ ውስጥና ከውጪ የሚመለከተው የንግድ ማህበረሰብ አስተያየት በማካተትና የነበረው የአሰራር ስርዓት በማሻሻል ይህ አሠራር የተዘጋጀ በመሆኑ ታይቶ እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲደረግ የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

# በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር ማስፈፀሚያ የአሰራር ማኑዋል

ጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## መግቢያ

የጉምሩክ አዋጅ ዕቃዎች ለተለያየ ምክንያት በጊዜያዊነት ወደሀገር ሲገቡ እንደሚችሉ የሚደነግግ ሲሆን ኮንቴነር ዕቃ በማሸግ ለተደጋጋሚ አገልግሎት የሚውል በመሆኑ እንደማንኛውም ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ በታሪፍ አመዳደብ ደንብ መሰረት ምጣኔ ተጥሎበት ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብበት የሚችል ዕቃ ነው፡፡

ስለሆነም በዕቃ መያዣነት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ኮንቴነር ተመልሶ ከአገር ስለመውጣቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ለቀረጥና ታክሱ ዋስትና የሚያዝበት፤ ኮንቴነሩ ከአገር መውጣቱ ወይም የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ወኪል ወይም ደረቅ ወደብ ኮንቴነር ተርሚናል መረከባቸው ሲረጋገጥ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ የሚደረግበት እንዲሁም ላኪዎች የኮንቴነር እጥረት እንዳያጋጥማቸው ከአስመጪዎች፤ ከመርከብ ድርጅቶችና ከመርከብ ወኪሎች ሊረከቡ የሚችሉበት ይህ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## <u>አጠቃላይ</u>

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ የአሰራር ስርዓት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር ለማስፈፀም የተዘጋጀ የአሰራር ሥርዓት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ በሌላ ሕግ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የአሰራር ማኑዋል ውስጥ፡-

1) **"ኮንቴነር"፡-** ማለት ለደረቅ ወይም ቅዝቃዜ ለሚፈልጉ ዕቃዎች ማሸጊያነት ለተደጋጋሚ አገልግሎት እንዲውል ተደርጎ የተሰራ ሆኖ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሚሆኑ የማጓጓዣ ዓይነት ዕቃን ለማጓጓዝ በሚመች በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ዝርግ፣ ክፍት ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዝግ የሆነ በቀላሉ ዕቃን ለመጫንና ለማውረድ የሚያስችል የደረቅ ወይም የፈሳሽ ጭነት መያዣ ሲሆን ከኮንቴነሩ ጋር ተነጥለው ሊታዩ የማይችሉ አክሰሰሪዎቹንም ይጨምራል፡፡

2) **"በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገባ ኮንቴነር"** ፡- ማለት ዕቃ ታሽጎበት ወይም በባዶ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ በዚህ የአሰራር ስርዓት ትርጉም የተሰጠው ኮንቴነር ነው፡፡

3) **"በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገባ ኮንቴነር የጉምሩክ አሰራር ስርዓት"**፡- ማለት በዕቃ መያዣነት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ኮንቴነር ወይም የዕቃ መጠቅለያ ላይ የሚፈፀም የጉምሩክ አሰራር ሥርዓት ሲሆን ኮንቴነሩ የገቢ ዕቃ ይዞ ወደ አገር ሲገባ ወይም የወጪ ዕቃ ይዞ ከአገር ሲወጣ ወይም ባዶውን ወደ አገር ሲገባ ወይም ከአገር ሲወጣ የሚፈፀም የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት ሂደት ነው፡፡

4) **"የመርከብ ወኪል"**፡- ማለት በኢትዮጵያ ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ፈቃድ የተሰጠው እና ከየትኛውም የመርከብ ድርጅት የውክልና ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል ወኪል ነው፤

5) **"የደረቅ ወደብ አስተዳደርና ኮንቴነር ተርሚናል"** ፡- ማለት በኢትዮጵያ ማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ፈቃድ የተሰጠው ዕቃዎች ወደ ውጭ አገር የሚጫኑበትና ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የሚራገፉበት ቦታ ነው፡፡

6) **"አምራች"**፡- ማለት ጥሬ እቃዎችን ከውጭ ሃገር በማስመጣት ወይም የሃገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም በሃገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት በሚፈጥር ማንኛውም ምርት የማምረት ወይም የመገጣጠም ሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ፤ ለሃገር ውስጥ ፍጆታ ወይም ለውጭ ንግድ ዓላማ የሚያመርት ድርጅት ነው፡፡

7) **"ላኪ"**፡- ማለት ከዕቃ ጋር ያስገባውን፤ ከአስመጪ ወይም ከመርከብ ድርጅት ወይም ከመርከብ ወኪል የተረከበውን ኮንቴነር የወጪ ዕቃ እንዲጫንበት በማድረግ ከአገር የሚያስወጣ ላኪ ነው፡፡

8) **"አምራች ላኪ"**፡- ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ፤ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

9) **"አስመጪ"**፡- ማለት እቃ ከውጭ ሃገር አስመጥቶ ለሃገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርብ ድርጅት ነው፡፡

10) **"የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች"**፡- ማለት በዓለም አቀፍ ንግድ አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሆነና በኮሚሽኑ የተዘጋጁ መስፈርቶችን በማሟላት በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የታቀፈ ድርጅት ነው፡፡

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs

11) **"ዋስትና"፡-** ማለት በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገባ ኮንቴነር በዚህ የአሰራር ሥርዓት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣቱ እስኪረጋገጥ ድረስ በጉምሩክ የሚያዝ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም የባንክ ጋራንቲ ወይም የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ወይም በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ነው፡፡

12) **"በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት"፡-** ማለት ኮንቴነሩን በጽሁፍ ግዴታ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ በተፈቀደለት ድርጅት የበላይ ኃላፊ ተፈርሞ የሚቀርብ የስምምነት ደብዳቤ ነው፡፡

13) **"የጊዜ ገደብ"** ፡- ማለት በጊዜያዊት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ወደ አገር ከገባበት ቀን ጀምሮ ተመልሶ ከአገር እስኪወጣ ድረስ በዚህ መመሪያ መሰረት የተፈቀደ አገር ውስጥ የመቆያ ጊዜ ማለት ነው፤

14) **አዋጅ** ፡-ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና 1160/2011(እንደተሻሻለ) ነው፡፡

15) **ኮሚሽን እና ኮሚሽነር፡-** ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን እና የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ማለት ነው፡፡

16) በዚህ የአሰራር ሥርዓት ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላቶች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የአሰራር ስርዓት በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገቡ ኮንቴነሮችን በተመለከተ የሚቀርቡ ሠነዶች፣ ኮንቴነሮቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ከአገር መውጣታቸውን ለማረጋገጥ የሚያዝ የዋስትና ዓይነት፣ በአገር ውስጥ የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ እንዲሁም የተያዘው ዋስትና ገቢ የሚደረግበት እና ተመላሽ የሚደረግበት ሁኔታ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>ስለዋስትና</u>

### 4. የዋስትና ዓይነቶች

በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ ኮንቴነር ከአገር መውጣቱን ለማረጋገጥ በጉምሩክ ሊያዙ የሚችሉ የዋስትና ዓይነቶች፡-

(ሀ) የጥሬ ገንዘብ ዋስትና፤

(ለ) የባንክ ጋራንቲ፤

በኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No 1
Ethiopia Customs Commission

(ሐ) የመድህን ዋስትና፣ እና

(መ) በጽሑፍ በተደረገ የግዴታ ስምምነት ናቸው

## 5. ስለ ዋስትና አያያዝ

1/ በደብዳቤ ዋስትና ወይም በጽሑፍ በተደረገ የግዴታ ስምምነት ኮንቴነር በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚያስገቡ ድርጅቶች፡-

ሀ) የመርከብ አጓጓዥ ድርጅቶች ወይም የመርከብ ወኪሎች፤

ለ) ኤምባሲዎች፤ ቆንስላ ጽ/ቤቶች፤ አለም አቀፍ ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ተቋማትና ሰራተኞች፤

ሐ) የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች፤ አምራች፤ አምራች ላኪዎች፣ ላኪዎች ወይም በአምራች ላኪ ወይም ላኪ ስም ዕቃ ሳይዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ባዶ ኮንቴነር፤

መ) በኮንቴነር ተርሚናል እና ወደብ አስተዳደር ስራ ላይ የተሰማሩ በህግ የተፈቀደላቸው አካላት፤

ሠ) የመንግስት መ/ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤

ረ) ከመንግስት መ/ቤቶች እና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ጋር በፕሮጀክት የውል ስምምነት ዕቃ ይዞ በግል ድርጅት ስም በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ኮንቴነር፤

2/ ማንኛውም አስመጪ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባው ኮንቴነር በአገር ውስጥ የሚቀበለው የመርከብ ወኪል ያለው መሆኑ ደብዳቤ ወይም Container Interchange Receipt-In (CIR) ሲያቀርብ በጽሑፍ ግዴታ ደብዳቤ ለመስተናገድ ይፈቀድለታል፤

3/ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ኮንቴነር የመርከብ ወኪል ባይኖረውም ፈቃድ የተሰጠው ኮንቴነር ተርሚናል እና የወደብ አስተዳደር ኮንቴነሩ በአገር ውስጥ እንደሚረከበውና ኃላፊነቱ እንደሚወስድ በጽሑፍ ማረጋገጫ ለጉምሩክ ካቀረበ በጽሑፍ በተገባ ግዴታ ወይም በደብዳቤ ለመስተናገድ ይፈቀድለታል፤

4/ በተራ ቁጥር 5 ንዑስ ቁጥር 1 ፤ 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች የሚያቀርቡት የደብዳቤ ዋስትና ተቀባይነት የሚያገኘው በጊዜያዊነት ዕቃ ይዞ ወይም በባዶ ወደ አገር ውስጥ የገባው ኮንቴነር በዚህ የአሰራር ማኑዋል በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም

በግልፅ ተወስኖ በጽሑፍ በተሰጠው ተጨማሪ አገር ውስጥ የኮንቴነር የማቆያ ጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ኮንቴነሩን ከአገር ለማስወጣትና ኮንቴነሩ ያላስወጣ እንደሆነ ቀረጥና ታክሱን ለመክፈል ኃላፊነት በመውሰድ በተቋሙ የበላይ ሀላፊ ተፈርሞ ሲቀርብ ይሆናል፡፡

5/ በተራ ቁጥር 5 ንዑስ ቁጥር 1፣ 2 እና 3 ከተገለፀው ውጪ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ኮንቴነር የሚያዘው ዋስትና የቀረጥና ታክሱን መጠን በጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና ይሆናል፡፡

6/ በጊዚያዊነት ወደ ሀገር ገብቶ ለሚወጣ ኮንቴነር የሚጠየቀው ዋስትና በዕቃ አስተላላፊው ሊቀርብ ይችላል፡፡

7/ በተደጋጋሚ ጊዜ ኮንቴነር በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው በየዓመቱ የሚታደስ የተጠቃለለ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## <u>የጊዜ ገደብ</u>

### 6. ኮንቴነር በአገር ውስጥ የመቆያ የጊዜ ገደብ

1/ ለመደበኛ አስመጪ የሚፈቀድ የጊዜ ገደብ

ሀ) በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ኮንቴነር ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣት አለበት፤

ለ) ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ኮንቴነር ወደ አገር ውስጥ ገባ የሚባለው ወደ መዳረሻ ጣቢያ ደርሶ ትራንዚት ካጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

2/ ለመርከብ ድርጅት ወይም ለመርከብ ወኪል የሚፈቀድ የጊዜ ገደብ

ሀ) ማንኛውም የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ወኪል በዩኒሞዳል የትራንስፖርት ስርዓት ወደ አገር የገባን ኮንቴነር ከአስመጪዎች ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ከአገር ማስወጣት አለበት፤

ለ) ለወጪ ዕቃ ማጓጓዣ የኮንቴነር እጥረት ለማቃለል በመርከብ ወኪል ማረጋገጫ በጊዜያዊነት ከውጭ የሚገባ ባዶ ኮንቴነር ወደ መዳረሻ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደርሶ ትራንዚት ካጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 3 ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣት አለበት፤

3/ ኮንቴነሩ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣት የማይችል መሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አገር ውስጥ እያለ የመቆያ ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ሊራዘም ይችላል። ሆኖም የሚራዘመው ጊዜ ከ3 ወር ሊበልጥ አይችልም።

4/ ከአንድ ጊዜ በላይ ተጨማሪ ማራዘሚያ የሚያስፈልግ መሆኑ በቂ ማረጋገጫ ከቀረበ በኮሚሽኑ ኦፕሬሽን ዘርፍ በልዩ ሁኔታ ሊራዘም ይችላል።

5/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባው ኮንቴነር በህግ ስልጣን ባለው አካል በመያዙ ምክንያት ተመልሶ ከአገር መውጣት ያልቻለ እንደሆነ ጉዳይ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ አገር ውስጥ ሊቆይ ይችላል። ሆኖም የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ መውጣት አለበት።

6/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማሳወቅ በየትኛውም የጉምሩክ መውጫ በር በኩል መውጣት ይችላል።

## 7. ባዶ ኮንቴነር በጊዜያዊነት ስለማስገባት

1/ ለወጪ ዕቃ ማጓጓዣ የኮንቴነር እጥረት ለማቃለል በመርከብ ወኪል ማረጋገጫ በጊዜያዊነት ከውጭ የሚገባው ባዶ ኮንቴነር ቀለል ባለ የኮንቴነር ዲክላራሲዮን ተሞልቶ እንዲገባ በኮሚሽኑ ሊፈቀድ ይችላል፤

2/ ኮንቴነር የወጪ ዕቃ ታሽጎበት ከአገር በሚወጣበት ጊዜ ኮንቴነሩ ተመልሶ መውጣቱን ለማረጋገጥ የወጪ ዕቃ የተመዘገበበት ዲክላራሲዮን ኮንቴነሩ በጊዜያዊነት ከገባበት ዲክላራሲዮን ጋር መናበብ አለበት፤

3/ ባዶ ኮንቴነር በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብቶ ተመልሶ ሲወጣ የአገር ውስጥ ቆይታው በዚህ የአሰራር ሥርዓት በተደነገገው ጊዜ ገደብ መሰረት ይሆናል።



የኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission

## 8. ኮንቴነር ተመልሶ መውጣቱን ስለማረጋገጥ

1/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ዕቃ ጭኖ የገባ ኮንቴነር የወጪ ዕቃ ጭኖ የሚወጣ እንደሆነ መውጫ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ይህንኑ በማረጋገጥ በሲስተም (በዲክላራሲዮኑ/T1) ለመነሻ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መረጃ መተላለፍ አለበት፤

2/ ዕቃ ይዞ ወደ አገር የገባ ኮንቴነር በባዶ ተመልሶ ከአገር የሚወጣ እንደሆነ ቀድሞ ወደ አገር ውስጥ የገባበት የመንገድ ወረቀት (IM8 ወይም T1) በመጠቀም መውጫ በር የሚገኘው የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮንቴነሩ መውጣቱን በማረጋገጥ ለመነሻ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መረጃ በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት በኩል መተላለፍ አለበት፤

3/ የጉምሩክ ሲስተም በሚቋረጥበት ጊዜ ኮንቴነሩ ተመልሶ ከአገር መውጣቱን የሚገልፅ ማረጋገጫ ከጉምሩክ የመውጫ በር ቅ/ጽ/ቤት/ጣቢያ ወይም የጅቡቲ የኮንቴነር ተርሚናል ኦፐሬተር ኮንቴነሩን ስለመረከቡ በማህተም የተረጋገጠበት ማስረጃ ዋስትና ያስያዘው አካል ወይም የዕቃው አስመጪ ለመነሻ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

## 9. በጊዜያዊነት የገባ ኮንቴነር በሀገር ውስጥ ስለሚቀርበት ሁኔታ

1/ ወደ አገር ውስጥ የገባ ጉዳት የደረሰበት ኮንቴነር በመርከብ ድርጅቱ ወይም በመርከብ ወኪል አቅራቢነትና አረጋጋጭነት ማስረጃ ሲቀርብ በዚህ የአሰራር ስርዓት መሰረት በሀገር ውስጥ ሊቀር ይችላል፤

2/ በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የገባ ኮንቴነር በሚመለከተው አካል በአገር ውስጥ እንዲቀር ፍቃድ ያገኘ እና ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት እንደሆነ በሀገር ውስጥ ሊቀር ይችላል፤

3/ በአገር ውስጥ እንዲቀር ፍቃድ ያገኘ እና ከቀረጥና ታክስ ነፃ የተፈቀደ እንደሆነ በጊዚያዊነት የገባ ኮንቴነር በሀገር ውስጥ ሊቀር ይችላል፤

## 10. የተያዘ ዋስትና ተመላሽ ስለማድረግ

1/ በዚህ የአሰራር ሥርዓት በተገለፀው የጊዜ ገደብ መሰረት በጊዜያዊነት የገባ ኮንቴነር ተመልሶ ከአገር መወጣቱ የተረጋገጠ እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል፤

2/ በአስመጪ በጊዜያዊነት የገባው ኮንቴነር በዚህ የአሰራር ስርዓት ኮንቴነር በሀገር ውስጥ እንዲቆይ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመርከብ ድርጅት ወይም መርከብ ወኪል ወይም ኮንቴነር ተርሚናል እና ወደብ አስተዳደር የተረከበው መሆኑ ደብዳቤ ወይም የContainer Interchange Receipt (CIR) ከቀረበ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል፤

3/ በጊዜያዊነት የገባው ኮንቴነር ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በጉምሩክ የተረጋገጠና በዚህ የአሰራር ማኑዋል መሰረት ከጉዳት በቀረው ላይ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት እንደሆነ ወይም ሙሉ ለሙሉ በመውደሙ የተወገደ እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል፤

## 11. የተያዘ ዋስትና ገቢ ስለሚደረግበት ሁኔታ

1/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ኮንቴነር በዚህ የአሰራር ሥርዓት በአገር ውስጥ እንዲቆይ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በግልፅ ተወስኖ በጽሑፍ በተፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ ወይም በዚሁ የአሰራር ሥርዓት መሰረት በሀገር ውስጥ ባዶ ኮንቴነር ከአስመጪ ለሚረከብ የመርከብ አጓጓዥ ድርጅት፤ ለመርከብ ወኪል፤ ለዕቃ ላኪ፤ ለኮንቴነር ተርሚናል እና ለወደብ አስተዳደር ያላስተላለፈ እንደሆነ እና ለዚሁ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ አይደረግም::

2/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ኮንቴነር በዚህ የአሠራር ሥርዓት ከተፈቀደው የጊዜ ገደብ ተላልፎ ከአገር እንዲወጣ ቢደረግም የተያዘው ዋስትና ተመላሽ አይደረግም::

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs

# ምዕራፍ አራት

## ተግባር እና ኃላፊነት

### 12. የአስመጪው ግዴታ

1/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባና ዋስትና የተያዘበት ኮንቴነር በዚህ የአሰራር ሥርዓት በተወሰነው ጊዜ ገደብ ወይም በተራዘመው ጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ማስወጣት ወይም ለመርከብ ወኪል ወይም ለወጪ ዕቃ ላኪ ያስረከበ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

2/ ኮንቴነር ባዶውን ከአገር የወጣ እንደሆነ ቀድሞ ዕቃ ይዞ ወደ አገር የገባበት ዲክላራሲዮን ላይ ኮንቴነሩ ከአገር ስለመውጣቱ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት እንዲረጋገጥለት አስመጪው ለመውጫ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መጠየቅ አለበት፤

3/ አስመጪው ኮንቴነሩን ለመርከብ ወኪል ወይም ለወጪ ዕቃ ላኪ አስረክቦ ከሆነ ስለማስረከቡ የኮንቴነሩ መረጃ የያዘ ማረጋገጫ የደብዳቤ ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

### 13. የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ድርጅት ወኪል ግዴታ

1/ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከጭነት ጋር ያስገባው ወይም ከአስመጪ የተረከበውን ወይም ለወጪ ዕቃ ማጓጓዣ የኮንቴነር እጥረት ለማቃለል በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ባዶ ኮንቴነር እስከ ሶስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ አለበት፤

2/ በተራ ቁጥር 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጭነት ጋር ወደ አገር የገባው ወይም ከአስመጪ የተረከበው ኮንቴነር፡-

ሀ) በመልቲ ሞዳል ወደ አገር የገባ ከሆነ ሲገባ የተመዘገበበት IM8/T1 ላይ ኮንቴነሩ ስለመውጣቱ በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት እንዲረጋገጥ ለመውጫ በር የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥያቄ መቅረብ አለበት፤

ለ) በዩኒ ሞዳል ወደ አገር ከሆነ ገቢ ዲክላራሲዮን ላይ ኮንቴነሩ ስለመውጣቱ በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት እንዲረጋገጥ ለመውጫ በር የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥያቄ መቅረብ አለበት፤

3/ የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ድርጅት ወኪል ከጭነት ጋር ያስገባው ወይም ከአስመጪ የተረከበው ባዶ ኮንቴነር ለወጪ ዕቃ ላኪ የሚያስረክብ ከሆነ ኮንቴነሩ ወደ አገር ሲገባ የተመዘገበበትን ዲክላራሲዮን ጨምሮ የተሟላ መረጃ ለላኪው መስጠት አለበት፤

4/ የመርከብ ድርጅቱ ወይም የመርከብ ወኪሉ ለወጪ ዕቃ ማጓጓዣ የኮንቴነር እጥረት ለማቃለል በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ኮንቴነር የወጪ ዕቃ ለማሸግ ለላኪ ሲያስረክብ የላኪው ስም፣ የኮንቴነር ቁጥር እና በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የገባበት ዲክላራሲዮን ቁጥር መረጃ የደብዳቤ ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

5/ በዚህ በዚህ የአሰራር ሥራዓት ተራ ቁጥር 12 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመርከብ ድርጅቱ ወይም የመርከብ ድርጅት ወኪሉ ለዕቃ ላኪ ያስረከባቸውን ባዶ ኮንቴነሮች የላኪው ስም፣ የኮንቴነር ቁጥር እና ወደ አገር የገባበት የመንገድ ወረቀት ወይም የዲክላራሲዮን ቁጥር መረጃ ለኮሚሽኑ የትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በየወሩ ማቅረብ አለበት፤

## 14. የወጪ ዕቃ ላኪ ግዴታ

1/ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ከጭነት ጋር ያስገባው ወይም ከአስመጪ ወይም ከመርከብ ድርጅት ወይም ከመርከብ ወኪል የተረከበው ወይም ለወጪ ዕቃ ማሸጊያነት በጊዜያዊነት ያስገባው ባዶ ኮንቴነር ከተረከበው ወይም ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃ በማሸግ መልሶ ከሀገር ማስወጣት አለበት፤

2/ የወጪ ዕቃ ላኪው በተረከበውን ኮንቴነር ዕቃ አሽጎ ወደ ውጪ በሚልክበት ወቅት የወጪ ዕቃ ከተመዘገበበት ዲክላራሲዮን ጋር ኮንቴነሩ ወደ አገር የገባበትን ሰነዶች በማያያዝ ዋስትና ላስያዘበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

3/ በጊዜያዊነት ባዶም ሆነ ዕቃ የያዘ ኮንቴነር ወደ አገር ያስገባውን ወይም የተረከበውን የወጪ ዕቃ አሽጎ በሚልክበት ጊዜ ኮንቴነሩ ከአገር ስለመውጣቱ በወጪ ዲክላራሲዮን ላይ በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት በኩል እንዲረጋገጥለት ለመውጫ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መጠየቅ አለበት፤

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission

## 15. የትራንዚትና የመጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት

1/ የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ድርጅት ወኪል ከአስመጪ የተረከበውን ኮንቴነር መረጃ በየወሩ እንዲያደራጅ በማድረግ ለላኪዎች እንዲያደርስ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

2/ የመርከብ ድርጅቶች ወይም የመርከብ ድርጅት ወኪሎች ለላኪዎች ያስረከቧቸውን ኮንቴነሮች መረጃ ለሚመለከታቸው የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲያደርስ በማድረግ በጊዚያዊነት የገባ ኮንቴነር ተመልሶ ስለመውጣቱ እንዲረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3/ በአስመጪዎች፣ በላኪዎች፣ በመርከብ ድርጅቶች እና በመርከብ ድርጅት ወኪሎች መካከል የሚደረግ የባዶ ኮንቴነር ርክክብ ዙሪያ የሚገጥሙ ችግሮች ላይ መፍትሄ ይሰጣል፣ የውሳኔ ሀሳብ ለኦፐሬሽን ዘርፍ ያቀርባል፡፡

4/ ከጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት፣ ከገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እና ከአምራችና ወጪ ዕቃ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ጋር በመቀናጀት ባዶ ኮንቴነር ወደ አገር በጊዚያዊነት በሚገባበትና በሚወጣበት ሂደት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 16. የመነሻ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊነት

1/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ባዶም ሆነ ዕቃ የያዘ ኮንቴነር የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈፅሞ ተመልሶ ከአገር ሲወጣ በሲስተም በማረጋገጥ የተያዘውን ዋስትና ተመላሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ከአገር መውጣቱን በሲስተም ማረጋገጥ የማይቻል ከሆነ ከመውጫ የጉምሩክ ጣቢያ በፋክስ ወይም በኢ-ሜል ወይም በደብዳቤ በመጠየቅ ወይም አስመጪው ኮንቴነሩ ከሀገር ስለመውጣቱ ቀድሞ ማስረጃ በማቅረብ ካረጋገጠ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ያደርጋል፤

3/ አስመጪዎች፣ ላኪዎች፣ የመርከብ ድርጅቶች፣ የመርከብ ድርጅቶች ወኪሎች፣ ደረቅ ወደብ እና የኮንቴነር ተርሚናል በመካከላቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ አስረካቢው አካል የሰጠው ዋስትና እንዲነሳለት ወይም እንዲመለስለት ያደርጋል፤

4/ አስመጪዎች፤ ላኪዎች፤ የመርከብ ድርጅቶች፣ የመርከብ ድርጅት ወኪሎች ባዶ ኮንቴነር ዝውውር መረጃ በማስቀረብ የተጣለባቸውን ግዴታዎች መወጣታቸውን ያረጋግጣል፤

5/ ዋስትና ተይዞበት ወይም በግዴታ ደብዳቤ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር በሌላ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል የወጪ ዕቃ ጭኖ ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከቀረበ ወይም በሲስተም ከተረጋገጠ የተያዘው ዋስትና መመለስ ይኖርበታል፤

**17. የመውጫ በር ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊነት**

1/ የወጪ ዕቃ የያዘ ወይም ባዶውን ከአገር የሚወጣ ኮንቴነር በጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት (በዲክላራሲዮኑ/T1) በመጠቀም ስለመውጣቱ ማረጋገጥ አለበት፤

2/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ከአገር መውጣቱን በሲስተም ማረጋገጥ የማይቻል ከሆነ ኮንቴነሩ ከአገር ስለመውጣቱ ለመነሻ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በፋክስ ወይም በኢ-ሜል ወይም በደብዳቤ ያሳውቃል፤

3/ ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮንቴነሩ ከሀገር ወጥቶ በተለያየ ምክንያት በመውጫ በር ማረጋገጫ ያልቀረበበት ቢሆንም የመርከብ ድርጅቱ ኮንቴነሩ ስለመረከቡ ማረጋገጫ የሰጠበት እንደሆነ የቀረበው ማረጋገጫ ትክክለኛነት እስከተረጋገጠ ድረስ ኮንቴነሩ እንደወጣ ተቆጥሮ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ይደረጋል።

## ምዕራፍ አምስት

## <u>ልዩ ልዩ ሁኔታዎች</u>

**18. ስለ ጉዳት**

1/ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ኮንቴነር ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት በመርከብ ድርጅት ወይም በመርከብ ድርጅት ወኪል አቅራቢነትና አረጋጋጭነት ማስረጃ ቀርቦበት በአገር ውስጥ እንዲቀር በጉምሩክ ፈቃድ ካገኘ ተመልሶ ከሀገር እንዲወጣ አይገደድም።

2/ ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የገባ ኮንቴነር ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ አገር ውስጥ እንዲቀር ስልጣን ባለው አካል ፈቃድ የተሰጠበት እንደሆነ ኮንቴነሩ አገር ውስጥ ሊቀር ይችላል፡፡

3/ ዕቃ ጭኖ ወይም በባዶ በጊዜያዊነት ወደ አገር ሲገባ ወይም ተመልሶ በሚወጣበት ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ኮንቴነር ወደ ውጭ አገር መመለስ የማይችል መሆኑ ማረጋገጫ ቀርቦ የመድን ዋስትና ለመርከብ ድርጅቱ ወይም ለወኪሉ ሲከፈልና ከባለሙያ በሚቀርብ የጉዳቱ መጠን ማስረጃ መሰረት በቅሪተ አካሉ ላይ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲከፈልበት ቀደም ሲል ለኮንቴነሩ የተያዘው ዋስትና ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

4/ ጉዳት የደረሰበት ኮንቴነር የጉዳቱ መጠን የሚያሳይ ማስረጃ ከባለሙያ በማቅረብ በቅሪተ አካሉ ላይ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ባለቤቱ መረከብ ያልቻለ እንደሆነ ጉምሩክ ተረክቦ ወይም ባለበት ቦታ ሆኖ ኮንቴነሩን ሊያስወግደው ይችላል፡፡

## 19. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው አሰራሮች

1/ በቁጥር 3./732/09 ሰኔ 21 ቀን 2009 ዓ.ም የተላለፈው አሰራር በዚህ የአሰራር ሥርዓት ተተክቷል፡፡

2/ በእንጥልጥል ላይ ያሉና በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ኮንቴነሮች በዚህ የአሰራር ሥርዓት ማኑዋል መሰረት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

**የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን**